# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት
# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል**

**1. የዝናብ ሁኔታ**

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ መረጃ ካስተላለፉ 110 ወረዳዎች ወስጥ በ46 ወረዳዎች መጠኑ ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ስርጭቱ የዘነበባቸው ሁሉንም አካባቢዎች ያዳረሰ ዝናብ ያገኙ ሲሆን በ64 ወረዳዎች ዝናብ ያላገኙ እና በ4 ወረዳዎች በኔትወርክ መቆራረጥና በፀጥታ ችግር ምክንያት መረጃ ያልተገኘ መሆኑን ከክልሉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1 የበልግ ስራ እንቅስቃሴን በተመለከተ**

በ2014/15 በበልግ ወቅት በዓመታዊ በተለያዩ ሰብሎች እና አትክልት ለማልማት 990,902 ሄ/ር መሬት ዕቅድ ተይዞ በበልግ የማሳ ዝግጅት ሥራ በተመለከተ 1ኛ እርሻ 936,749ሄ/ር እና 2ኛ እርሻ 831,400ሄ/ር የታረሰ ሲሆን 645,256 ሄ/ር (69%) በዘር መሸፈኑን የተቻለ ቢሆንም የበልግ ዝናብ ከሚጠበቅበት ወቅት አጀማመሩ የዘገየና ሥርጭቱም የተቆራረጠ በመሆኑ የበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፤ ሆኖም በተወሰነ መልኩ የዘር ወቅቱ ወደፊት የገፋ ቢሆንም የዝናቡ ቀጣይነት እስካለ ድረስ የዘር ሥራውም የሚቀጥል መሆኑን ከሰብል ልማት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

**2.2. የፀረ-ሰብል ተባይ በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ በ2014 በልግ ወቅት በአገዳ ሰብሎች ከተሸፈነው 200,775 ሄ/ር ማሳ ላይ አዲስ መጤ ተምች በ2 ዞኖች (ደ/ኦሞና ጎፋ) እና 1 ልዩ ወረዳ (ባስኬቶ) 1,027 ሄ/ር ማሳ በበቆሎና በማሽላ ሰብል ላይ ተከስቷል፡፡ እየተሰራ ያለ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በኬሚካል 125ሄ/ር እና 618ሄ/ር በባህላዊ በድምሩ 743ሄ/ር በሳምንቱ መከላከል የተደረገ ሲሆን፤ በመደበኛ ተምች በ2 ዞኖች ደ/ኦሞ (በናፀማይ እና ሐመር) እና ኮንሶ (ካራት ዙሪያና ኮልሜ)1 ልዩ ወረዳ (አሌ) በበቆሎ.በማሽላ፣ በጤፍና ዳጉሳ በ22,154ሄ/ር ማሳ ላይ የተከሰተ ሲሆን 1,094ሄ/ር በኬሚካል፣ 4010ሄ/ር በባህላዊ በድምሩ 5,104 ሄ/ር ማሳ መቆጣተር ተችሏል፡፡ የዘንድሮ የበልግ ወቅት የዝናብ ሁኔታ በመጠንም በስርጭትም ያልስተካከለ በመሆኑ የአየሩ ሁኔታ ለተባይ መስፋፋት ምቹ

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው በሁሉም አካባቢዎች በየእለቱ የአሰሳና የቅኝት ሥራውን ተጠናክሮ እንዲቀጥሉ የሚመለከተው አካል ብርቱ ክትትልና ድጋፍ ያሻል፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ አብዛኛዉ አከባቢዎች መደበኛ ዝናብ ከማግኘታቸዉ ጋር ተያይዞ የዉሃ አቅርቦት ችግር ባይታይም በተለይም በቆላማ ወረዳዎች አካባቢ ከመኖ እጥረት የተሻሻለ ባለመሆኑ እና ተፈናቃይ ባለባቸው አካባቢዎች (ኮንሶ ዞን) የግጠሽና መኖ ሽሚያ በመኖሩ የእንስሳት አቋም ከመደበኛ በታች እንደሆነ የክልሉ ሪፖርት ያመላክታል፡፡

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በሳምንቱ በወረረሽኝ መልክ የተከሰተ የእንስሳት በሽታ ባይኖርም መደበኛ የእስሳት በሽታዎች ክስተት እና ከመኖ እጥረቱ ጋር ተያይዞ የሰዉነት አቋማቸዉ ከመደበኛ በታች የሆኑ እንስሳት ለበሽታ ተጋላጭነት እንዳያደርስ የሚመለከተው አካል ትኩረት በመስጠት በቂ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ይገባል፡፡

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

የኮቪድ 19 ወረረሽን አኳያ በክልሉ በጤና ቢሮ ቴሌግራም ገጽ የተለቀቀው መረጃ እንደሚያመላክተዉ ባለፉት 7 ቀናት ከ 30/07/14ዓ.ም. እስከ 06/08/14ዓ.ም. ድረስ በተደረገዉ ላብራቶሪ ምርመራ ተጨማሪ 13 ሰዎች(በሀላባ በ8 ሰዎች ፣ በወላይታ 2 ሰዎች፣ በሀዲያ በ1 ሰው ፣ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በ1 ሰው እና በጉራጌ ዞን በ1 ሰው) አዲስ የተያዙ ናቸዉ፡፡ በበሽታው እየተያዙ ሰዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ የሚገኝ በመሆኑ ሕብረተሰቡ አሁንም ሳይዘናጋ ከመንግስትና ከጤና ባለሙያዎች በየጊዜው የሚሰጡ ቅድመ-ጥንቃቄ ሕጎችን በዲሲፒሊን በመተግበር ሊከሰቱ የሚችሉ የበሽታ ተጋላጭነትን በመቆጣጠር የከፋ ጉዳት እንዳይከሰት መተባበር የሚገባ ሲሆን የክልሉ ሚዲያዎችም ሕብረተሰቡን በማስጠንቀቅ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

በወላይታ ዞን በሳምንቱ መረጃ እንደሚያመለተዉ የዳሞት ፑላሳ ወረዳ የወባ በሽታ 350 ኬዝ በአንድ ሳምንት በመሆኑ በሽታዉ በስፋት እየጨመረ በመሆኑ በጤና ተቋማት በኩል የክትትልና የመከላከል ስራዉ ትኩረት ልሰጥ ይገባል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በክልሉ በመኸር እና በመስኖ የለሙ ሰብሎች ደርሰው ለምግብ ፍጆታነት እየዋሉና ለገበያ በመቅረብ ላይ የሚገኙ በመሆኑ እና በልማታዊ ሰፍትኔት ፕሮግራም ለታቀፉ ተጠቃሚዎች ከጥር ወር ጀምሮ በገንዘብ ክፍያ እየተፈፀመ መሆኑና በ2013/14 ዓ/ም የመኸር ቅድመ- ምርት ግምገማ መሠረት የምግብ ክፍተት እንደሚገጥማቸው ከተለዩት 505,402 ተረጂዎች በ5ኛዉ ምዕራፍ የልማታዊ ሰፍትኔት የአደጋ ምላሽ ሰጪ/shock responsive/ ፕሮግራም የጥርና የካቲት ወር ቀለብ በገንዘብ እንዲሁም ለ812,433ተረጂዎች በዓይነት እህል ቀርቦ ተሰራጪቷል፡፡

በመካከለኛ ደረጃ የምግብ እጥረት ለተለዩ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ሕፃናት፣አጥቢና ነፍሰ-ጡር እናቶች በዓለም የምግብ ፕሮግራም በሚደገፈው የተጨማሪ ምግብ ፕሮግራም (TSFP) በመደበኛነት ድጋፍ ለሚቀርብላቸው 18 ወረዳዎች ውስጥ ለ14 ወረዳዎች (ሁምቦ ፣ማረቆ፣ ወይራዲጆ፣ሚቶ፣ ላንፉሮ፣ ካራትዙሪያ፣ ሠገንዙሪያ፣ኬና፣ ቃጫ ቢራ፣ ምስራቅ ባዳዋቾ፣ ሲራሮ ባዳዋቾ፣ በሎሶ ሶሬ፣ ቀዲዳጋሜላ፣ እና አዲሎ) ፣በትኩረት አንድ በተመደቡ 15 ወረዳዎች ወስጥ 13 ወረዳዎች (ሥልጢ፣ ምስራቅ ስልጢ፣ ምስራቅ መስቃን፣ ዳሰነች፤ ሐመር፣ በናፀማይ፣ ኛንጋቶም፤ማሌ፤ኪንዶ ዲዳዬ፤ዱጉና ፋንጎና ጠምባሮ፣ደረሼና አማሮ) እና በ8 IMAM ወረዳዎች ውስጥ 6 ወረዳዎች (ወናጎ፣ኮቾሬ፣ይርጋጨፌ፣ኧሌ፣ኡባደብረፀሀይ እና ዛላ ) በድምሩ በ33 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኝ 57,6562 ሕፃናትና 65, 253 አጥቢና ነፍሰጡር እናቶች በጠቅላላው 12,815 ተጠቃሚዎች 6,621 ኩ/ል የሚያዝያ ወር አልሚ ምግብ ሥርጭት በየወረዳዎቹ በሚገኙ ማሰራጫ ጣቢያዎች እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በዚህ ሳምንት ጎፋ ዞን፣4 ልዩ ወረዳዎች (በስኬቶ፣ ደራሼ፣ አማሮ እና ቡርጂ) ጤና መረጃ ያልደረሰ ቢሆንም ከ10 ዞኖችና 2ልዩ ወረዳ (አሌ እና አማሮ) የተሰበሰቡ የጤና መረጃዎች የሚያመላክተው ከባለፈዉ ሳምንት ጋር ሲነፃር በክልሉ በምግብ እጥረት/አለመመጣጠን በሚመጣ በሽታ ምክንያት ወደ ሕክምና የገቡ ተመላላሽና የተኝቶ ታካሚ አዲስ ሕፃናት ከ1021ወደ 1693(39.7%)የጨመረ ሲሆን ከጠቅላላው ወደ ሕክምና ከገቡት ህፃናት ውስጥ 1559 (92%) ወደ ተመላላሽ እና 134(8%) ወደ ተኝቶ መታከም የገቡ ናቸው፡፡ ለአብነት በሳምንቱ ወደ ተመላላሽና ተኝቶ መታከም (OTP & SC ) የገቡ ህጻናት ቁጥር የመጨመር ሁኔታ የታየባቸው ዞኖች ከምባታ ጠምባሮ ዞን ቃጫ ቢራ ወረዳ ከ18 ወደ46፣ጌዲኦ ዞን ገደብ ወረዳ ከ2 ወደ 63፤ጋሞ

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

ዞንጋርዳ ማርታ ወረዳከ0 ወደ 92 እና ገረሴ ወረዳ ከ6 ወደ 307፣ ደ/ኦሞ ዞን ማሌ ወረዳ ከ0 ወደ31 እና ሳላማጎ ወረዳ ከ0 ወደ 84የጨመረ ሲሆን በመጠኑ የቀነሰ ወላይታ ዞን ቦሎሶ ሶሮ ወረዳ ከ58 ወደ 20 እና ሁምቦ ከ32 ወደ 3 ፤ ሀዲያ ዞን ከ29 ወደ 11 መሆኑን ከክልሉ የተገኘዉ መረጃ ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ የተመላላሽ እና ተኝተው ታካሚዎች ቁጥር ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻፀር የጨመር ሁኔታ የታየ ሲሆንበተለይ በሣምንቱ ወደ ተመላላሽ መታከሚያ የገቡ ህጻናት ቁጥር የመጨመር አዝማሚያ በመታየቱ ከዕለት ዕርዳታ አቅርቦትና ሥርጭት፣ የሕጻናትና የእናቶች አያያዝ ሁኔታ፣ የልየታ ጥራት፣ የአመጋገብ ሥርዓት… ወ.ዘ.ተ. ምክንያቶችን ለይቶ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ክትትል ድጋፍ ማድረግ ምላሽ መስጠትና ችግሩን መቀነስ ይገባል፡፡

**4.3 የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በሚመለከት**

በክልሉ በአብዘኛዉ አከባቢዎች መደበኛ ዝናብ የዘነበ በመሆኑ ብዙም የዉሃ እጥረት ችግር እየቀረበ አይደለም፡፡ ሆኖም በተወሰኑ ኪስ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃ ችግር ተጋላጭ ሆነው በመደነኛነት በተከታታይ እየቀረበላቸው ያሉ(ደ/ኦሞ፣ሀላባ፣እና ወላይታ)መሆኑ ይታወቃል፡፡ ደቡብ ኦሞዞን ለዳሰነች እና ለኛንጋቶም ወረዳዎች አንድ አንድቦቲ ውሃ እየቀረበ ያለው ተደራሽ ባለመሆኑ የክልሉ ውሃ ቢሮ ትኩረት ቢሠጥበት፡፡ ከተቋማት ብልሽትና የዉሃ ጥራት ጉድለት ጋር ተያይዞየሚከሰቱ ችግሮችን በተለይም ግጭትና ተፈናቃይ አካባቢዎችን በመለየት አስፈላጊውን የጥገና እና የዉሃ ጥራት ማስጠበቂያ ግባዓቶችን የማቅረብ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ በሚደረገው ለመደበኛ ተረጂዎች የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ምላሽ በተመለከተ ለኮንሶ ፣ ለወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ ፣ሀዲያ ፣ሥልጤ ፣ደቡብ ኦሞ ሀላባ፣ጌዲኦ ፣ጉራጌ እና ጠምባሮ ዞኖች 764,776 ተረጂዎች የተመደበ 114,716.4 ኩ/ል እህል የቀረበ 100092.5ኩ/ል(87%) ሲሆን ለተፈናቃይ ለኮንሶ ፣ሀዲያ ፣ስልጤ ፣ጉራጌ ፣ከ/ጠምባሮ እና ደ/ኦሞ ዞኖች 138049 ተረጂዎችየተመደበ 20707.35 ኩ/ል እህል የቀረበ 11693 ኩ/ል(56%) ሲሆን ባጠቃላይ የመደበኛ እና የተፈናቃይ ተረጂዎች ለ902825 ተረጂዎች 135423.75ኩ/ል ተመድቦ 111785.5ኩ/ል (83%) ቀርቧል፡፤

- በኮንሶ ዞን በ2014ዓ.ም. በተከሰተ ድርቅ ምክንያት ለ88184ወገኖች ምላሽ የተሰጠ ሲሆን እስከ 27/07/14 ዓ.ም. ድረስ ለካራት ዙሪያ ወረዳ መቅረብ ካለበት 6,209.1ኩ/ል ውስጥ እስከ ሚያዚያ 02/2014 ድረስ 4,030ኩ/ል እና በካራት ከተማ አስ/ር 100 ፐርሰንት ከቀረበው

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

900ኩ/ል ውስጥ እስከ ዛሬ ጠዋት 7,018ኩ/ል ለተለዩ ተጠቃሚዎች ማሰረጨት ተችሳDል። የሰገን ዙሪያ ወረዳ ደግሞ ሉልቱ መጋዘን ላይ መቅረብ ካለበት 4199.4ኩ/ል ውስጥ 1,272ኩ/ል ቀርቦ እስከ ዛሬ ቀን 04/08/14ዓ.ም. በሙሉ ተሰራጭቷል። በሰገን መጋዘን በኩል መቅረብ ያለበት በፀጥታ ችግር ምክንያት መቅረብ አልቻለም። ለካራት ዙሪያ ወረዳ ከቀረበው 4030ኩ/ል ውስጥ እስከ ዛሬ ሚያዚያ 04/08/14ዓ.ም. ድረስ 3,699ኩ/ል ለባዳይዴ፣ ፋጪማ፣ ሶሮቦ፣ ጎጫ፣ ገላቦ፣ ለሐይቴ፣ ትሽግሌና አባሮባ፣ ቀበሌያት ተሰራጭቷል።

- ኮንሶ ዞን በ2013/14ዓ.ም. መኸር ዳሰሳ ጥናት መነሻ ለካራት ዙሪያ ወረዳ 13,768፣ ለሰገን ዙሪያ ወረዳ 14,618 እና ለኬና ወረዳ 18,999 በድምሩ 47,385 ተረጂዎች በቀጣይ ወራት የአስቸካDይ ጊዜ የእለት እርዳታ እንደሚቀርብላቸው ከክልል ምላሽ በመሰጠቱ ምልመላውን እያጠናቀቁ ይገኛሉ።
- በጋሞ ዞን በቦረዳ ወረዳ የገባ 1057ኩ/ል ስንዴ፣ ቁጫ አልፋ ወረዳ 1308.05ኩ/ል ስዴ፣ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ 1455ኩ/ል ስዴ ተሰራጭል።
- በከምባታ ጠምባሮ ዞን መኸር 2012/13 ተረጂዎች 5ኛ ዙር ዕለት ርዳታና ቀለብ አቅርቦት በተመለከተ በወርልድ ቪዥን ለሚረዱ ወረዳዎች /ጠምባሮ፣ሀዳሮ ጡንጦ ቀዲዳ ጋሜላና ቃጫቢራ/ ወረዳዎች ቀርቦ ስርጭት መጠናቀቁ ታውቋል። እንዲሁም በመንግስት ፕሮግራም ከምቀርብላቸው ወረዳዎች ውስጥ ለአዲሎ ዙሪያ ወረዳ መቅረብ ከነበረት እህል 1164.3 ኩ/ል ውስጥ 726 ኩ/ል ብቻ ቀርቦ የቀረበዉ ተሰረጭቶ የተጠናቀቃ ሲሆን በተመሳሳይ አንጋጫ ወረዳ መቅረብ ከነበረበት እህል 1,466.25 ውስጥ 223 እንዲሁም ዳምቦያ ወረዳ መቅረብ ከነበረት 1500 ኩ/ል 224 ኩ/ል ብቻ ቀርቦ ተሰረጭቶ ተጠናቋል፡፤ ለዶዮገና ወረዳና ለሽንሽቾ ከተማ አስተደደር እስካሁን ምንም እርዳታ አቅርቦት እንደሌላ ለማወቅ ተችሏላ።
- በክልሉ በ2013/14 በልግ ምርት ግምገማ ለተለዩ ተጠቃሚዎች የዕለት እርዳታ ተሟልቶ ባለመቅረቡ፣እንዲሁም ድርቁ ባስከተለው የምግብ እጥረት የተጎዱ አካባቢዎችን ለመለየት በተደረገ ፈጣን ዳሰሳ ጥናት ለተለዩ 1,028,410 ተጠቃሚዎች ከተጠየቀው ድጋፍ ለ604,538 ተጠቃሚዎች እየቀረበ ያለ ሲሆን ይህም ድጋፍ ለተጠየቀላቸው ጠቅላላ ተጠቃሚዎች መቅረብ ከሚገባው 154,261.5 ኩ/ል እህል ውስጥ 65,378 ኩ/ል (42.4%)

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

የቀረበ ሲሆን ድጋፉ ለተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች መቅረብ ከሚገባው 90,680.7 ኩ/ል እህል አንፃር 65,378 ኩ/ል (72%) ቀርቦ በመሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ለተለዩ ተጠቃሚዎች በወቅቱና በሙሉ ፓኬጅ አለመቅረብ፣ በመካከለኛ የምግብ እጥረት በወቅቱ ለተለዩ ሕፃናት አጥቢና ነፍሰ-ጡር እናቶች የሚቀርበው ድጋፍ በወቅቱ ተደራሽ ካለማድረግ እና በክልሉ በአንዳንድ አካባቢዎች በከፋ የምግብ እጥረት/አለመመጣጠን ምክንያት በተመላላሽና ተኝቶ ታካሚዎች ቁጥር የመጨመር አዝማሚያ የምታይ በመሆኑ በአቅርቦት ላይ የሚታዩ ማነቆዎች በፌደራል ደረጃ ተፈትሾ ድጋፉ ለሁሉም ተጠቃሚዎች በወቅቱና በሙሉ ፓኬጅ ተደራሽ የምሆንበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

**6. ሌሎች አደጋዎች**

**6.1. የእሳት አደጋን በተመለከተ**

በባስኬቶ ልዩ ወረዳ በተከሰተ በጣለው በበልግ ዝናብ አማካይነት 577.5 ሄ/ር በበልግ የተዘሩ ሰብሎች ላይ በናዳና በጎርፍ ጉዳት አድርሷል፡፡ ከዚህም በተጨማር የ25 አ/አደሮች የመኖሪያ ቤቶችና በ3 ት/ቤቶች ጉዳት ሲያስከትል በሠፈራ ጣቢያ አካባቢ ያሉ ተማሪዎች ትምህርት የማማር ማስተማር ሂደት እንደተቋረጠ ዞን አደጋ መከላከል ፅ/ቤት በሳምንታዊ ሪፖርታቸው አካተተዋል፡፡ በሀላባ ዞን በሳምንቱ በድንገተኛ በእሳት አደጋ ክስተት ምክንያት በዌራ ወረዳ በኢሎለቃ ቀበሌ 2 የሳር ክዳን ቤቶችና በወይራ ዲጆ ወረዳ አንድ የሳር ክዳን ቤት በድምሩ በድምሩ በዞን 3 ቤቶች ከነሙሉ የቤት ንብረቶቻቸው የወረደመ መሆኑ፤ በዚህ ሳምንት በሀዲያ ዞን በተከሰተ ድንገተኛ የእሳት አደጋ ሚሻ ወረዳ ዋሶገበታ ቀበሌ 1 ጎምቦራ ወረዳ ወንዶ ቀበሌ 1፣ ጊቤ ወረዳ አውሶ ቀበሌ 10 ና አሊዋ ቀበሌ 1 በሻሸጎ ወረዳ 1 በድምሩ በዞኑ በሳምንቱ 14 የሳር ክዳን ቤቶች መቃጠላቸውን ከክልሉ የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

በኮንሶ ዞን በሰው ሠራሽ አደጋ ክስተት ምክንያት እስከ ግንቦት 4/09/2014 ዓ/ም ባለው መረጃ ከዞን በሳምንታዊ ሪፖርት የተላለፈው ከኮንሶ ዞን 6920 አ/ወራ፣917 እ/ወራ በድምሩ 7837 በቤተሰብ ወንድ 25,314 ሴት 25,308 በድምሩ 50,622 ወገኖች የተፈናቀሉ ሲሆን ከደራሼ ልዩ ወረዳ ከጋቶ ቀበሌ 6 ቀጠናዎች 1,942 አ/ወራ፣295 እማ ወራ በድምሩ 2,237 በቤተሰብ ወንድ 5,593 ሴት 5,816 በድምሩ 11,409 ወገኖች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በኮንሶ ዞን በካራት ዙሪያ ወረዳ፣ በዓይዴ ቀበሌ ማሳሌ ገበያ እና በትሽሌ ቀበሌ አተያና አየር ማረፊያ አካባቢ ይገኛሉ፡፡ ግጭቱ

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

ያስከተለው ጉዳት ባርጫ ቀበሌ በIRC አማካይነት የተገነባው ት/ቤና ባለሁለት ክፍል ጊዜያዊ መማሪያ ፣ በመለጋ ዱጋያ በመንግስት የተገነባው ሙሉ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት እና የቀበሌ አስተዳደር ፅ/ቤት እና በሰገን ዙሪያ ወረዳ በቾ ቀበሌ በእሳት ሙሉ በሙሉ የወደመ፡፤ ከዚህም በተጨማሪ በኮልሜ ክላስተር 2 ት/ቤቶች ፣ካራት ዙሪያ ወረዳ 7 ት/ቤቶች እና ሰገን ዙሪያ ወረዳ 11 ት/ቤቶች በድምሩ 20 ት/ቤቶች በፀጥታው ችግር ምክንያት ት/ቤቶች በመዘጋታቸው በት/ቤቱ ውስጥ ይማሩ የነበሩ ወንድ 5,626 ሴት 4,804 በድምሩ 10,430 ተማሪዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት መቀጠል አልተቻለም።

**7. የገበያ ሁኔታ**

**7.1 የእህል እና የእንስሳት ገበያ አቅርቦት እና የገበያ ዋጋን በተመለከተ**

የምግብ እህሎች የገበያ አቅርቦት ሁኔታን በተመለከተ በአብዛኛው አከባቢዎች በተለይ በዋና ዋና የምግብ እህሎች (ጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ እና ቦሎቄ) የአቅርቦት ውስንነት ያለ ቢሆንም ከዋጋ አንፃር ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለማቋረጥ ጭማሪ እያሳየ የሚገኝ በመሆኑ የሸማቹን አቅም እየተፈታተነ ይገኛል። ለአብነት የምግብ እህሎች ዋጋ ከባለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር በውስን አከባቢዎች ላይ መጠነኛ ጭማሪ ታይቷል። ለአብነት የስንዴ ገበያ ዋጋ በጎፋ ዞን ከብር 3608 ወደ ብር 3833(6%)፤በአማሮ ል/ወረዳ ከብር 3500 ወደ ብር 3800(8%)፤ በደቡብ ኦሞ ዞን ከብር 4220 ወደ ብር 4345 (3%) ጨምሯል። ጤፍ በሀዲያ ዞን ከብር 4616 ወደ ብር 4929(6%)፣አማሮ ልዩ ወረዳ ከብር 4100 ወደ 4500(9%) እና ደ/ኦሞ ዞን ከብር 5300 ወደ 5960(11%) ጭማሪ ታይቷል።በተመሳሳይ የእንስሳት ዋጋ ለአብነትየአንድ መካከለኛ በግ የገበያ ዋጋ በጎፋ ዞን ከብር 3980 ወደ ብር 5143 (29%) በሳምንቱ ውስጥ ጨምሯል።

በአጠቃላይ በተለይ በዋና ዋና የምግብ እህሎች (ጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ እና ቦሎቄ) የገበያ ዋጋ በተከታታይ ጭማሪ እያሳየ የመጣ በመሆኑ የሸማቹን አቅም እየተፈታተነ ይገኛል። በመሆኑም የገበያ ዋጋን ከማረጋገት አንፃር ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ንግድና ገበያ ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አካላት የቅርብ ክትትል የሚፈልግ ስለሆነ አማራጭ መፍትሄዎችን ማስቀመጥ ይሻል።

**ሠንጠረዥ 1 ዝርዝር የገበያ መረጃን በተመለከተ**

| ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | የገበያ ጊዜ | ሠ/ጤፍ | ስንዴ | በቆሎ | ቦሎቄ | በሬ | ላም | በግ | ፍየል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጋሞ | ባለፈው ሳምንት | 5013 | 3782 | 2950 | 2863 | 18628 | 13257 | 2750 | 3292 |
| | በዚህ ሳምንት | 5036 | 3827 | 2759 | 2891 | 19264 | 12864 | 2593 | 3277 |
| ጎፋ | ባለፈው ሳምንት | 5227 | 3608 | 2907 | 2666 | 23685 | 14300 | 3940 | 3620 |
| | በዚህ ሳምንት | 5240 | 3833 | 2820 | 3058 | 23542 | 14000 | 3980 | 3664 |

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጌዴኦ | ባለፈው ሳምንት | 5020 | 3714 | 2943 | - | 30000 | 20900 | 5143 | 4237 |
| | በዚህ ሳምንት | 5056 | 3838 | 2889 | -- | 31688 | 20038 | 5238 | 4583 |
| ሀዲያ | ባለፈው ሳምንት | 4616 | 3422 | 2720 | 3675 | 21162 | 13325 | 4180 | 3940 |
| | በዚህ ሳምንት | 4929 | 3645 | 2707 | 3180 | 20753 | 15610 | 3676 | 3899 |
| ከምባታ ጠምባሮ | ባለፈው ሳምንት | 4713 | 3506 | 2748 | 3467 | 20038 | 15363 | 3844 | 3513 |
| | በዚህ ሳምንት | 4725 | 3544 | 2756 | 3400 | 19950 | 15600 | 3875 | 3569 |
| ጉራጌ | ባለፈው ሳምንት | 4233 | 3653 | 2593 | - | 29813 | 19656 | 5088 | 4833 |
| | በዚህ ሳምንት | 4381 | 3564 | 2595 | -- | 29500 | 18875 | 4769 | 4767 |
| የም ል/ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 3960 | 3600 | 2520 | -- | 26600 | 15000 | 3500 | 4000 |
| | በዚህ ሳምንት | 3960 | 3240 | 2160 | -- | 26600 | 18000 | 4000 | 4500 |
| ወላይታ | ባለፈው ሳምንት | 4938 | 3830 | 2694 | 3619 | 19625 | 16125 | 3734 | 3566 |
| | በዚህ ሳምንት | 4895 | 3754 | 2684 | 3369 | 18975 | 15869 | 3744 | 3431 |
| ሀላባ | ባለፈው ሳምንት | 3916 | 3233 | 2383 | 2733 | 20211 | 11283 | 3710 | 4233 |
| | በዚህ ሳምንት | 3667 | 3233 | 2383 | 2717 | 20167 | 12500 | 3933 | 4367 |
| ስልጤ | ባለፈው ሳምንት | 4580 | 3244 | 2420 | - | 25927 | 18800 | 4050 | 4005 |
| | በዚህ ሳምንት | 4600 | 3250 | 2520 | -- | 25600 | 18850 | 4000 | 4000 |
| ኮንሶ | ባለፈው ሳምንት | 5200 | 4800 | 3600 | 3750 | 17000 | 8000 | 2200 | 2400 |
| | በዚህ ሳምንት | 5200 | 4800 | 3585 | 3750 | 17000 | 8000 | 2158 | 2225 |
| ደራሼ ል/ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 5000 | 3200 | 3200 | 4000 | 20000 | 15000 | 2500 | 3000 |
| | በዚህ ሳምንት | | | | | | | | |
| ኧሌ ል/ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 5000 | 3500 | 3500 | 3300 | 17000 | 70000 | 2500 | 3000 |
| | በዚህ ሳምንት | 5000 | 3500 | 3200 | 2600 | 17000 | 8000 | 3000 | 2800 |
| አማሮ ል/ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 4100 | 3500 | 2700 | 4000 | 26000 | 11000 | 7800 | 8100 |
| | በዚህ ሳምንት | 4500 | 3800 | 2700 | 4200 | 26000 | 11000 | 7800 | 8100 |
| ደቡብ ኦሞ | ባለፈው ሳምንት | 5630 | 4345 | 3145 | 2775 | 15775 | 9850 | 2580 | 2650 |
| | በዚህ ሳምንት | 5960 | 4425 | 3260 | 2950 | 21000 | 16075 | 3625 | 3150 |
| ቡርጂ ልዩ ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 5300 | 3600 | 2600 | 3100 | 23500 | 9300 | 2100 | 3800 |
| | በዚህ ሳምንት | | | | | | | | |
| ባስኬቶ ል/ወረዳ | ባለፈው ሳምንት | 4950 | 4700 | 3500 | -- | 21500 | 21100 | 6000 | 6500 |
| | በዚህ ሳምንት | 5000 | 4650 | 3725 | -- | 23100 | 22700 | 6500 | 7350 |

## ሲዳማ ክልል

### 1. የዝናብ ሁኔታ

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ በ16 ወረዳዎች መካከለኛ እስከ ዝቅተኛ ዝናብ የዘበነ ሲሆን በዝናብ ቀናት ብዛት በመጠንና በስርጭት ሲገመገም የሳምንቱ ዝናብ ዝቅተኛ ነበር፡፡ በዚህ ሳምንት የክልሉ አብዘኛ ወረዳዎች ዝናብ አላገኙም፡፡ ስለሆነም የዝናብ ሁኔታ ከመደበኛውና ከተለመደው የበልግ ወቅት አየር ንብረት ሁኔታ ጋር ተቀራራብነት የለለዉ በመሆኑ ለበልግ አምራች ወረዳዎች ከፍተኛ ስጋት እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1. የበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ**

በክልሉ የ2014/2015 ዓ/ም የበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የማሳ ዝግጅት ሥራና ዘር የመዝራት ሥራ እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን በ2014/15 ዓ/ም በልግ በዋና ዋና ሰብል ለማልማት 63,144 ሄ/ር (በቆሎ 59,496 ሄ/ር፣ ማሽላ 180 ሄ/ር እና ቦሎቄ 3,469 ሄ/ር) ማሳ የታቀደ ሲሆን እስከዚህ ሳምንት መጨረሻ **62,237** ሄ/ር (99%) ማሳ ታርሶ 51፣407 ሄ/ር(81.4%)ማሳ በዘር መሸፈኑን የእርሻ ዘርፍ ሪፖርት ያመለክታል፡፡

2.2 **የፀረ-ሰብል ተባይ በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ ስለ ፀረ-ሰብል ክስተት በተመለከተ አዲስ የደረሰን መረጃ የለም፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በአሁኑ ወቅት በክልሉ የበልግ ዝናብ መሻሻል ጋር ተያይዞ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ይታያል፡፡ በክልሉ በሁሉም ወረዳዎች በምባል ደረጃ የበልግ ዝናብ የመጣበት አዝማምያ እያሳየ መሆኑ ለእንስሳት ግጦሽና መኖ አቅርቦት በምፈለገው ደረጃ አጥጋቢ ባይሆንም አሁን ያለዉ የዝናብ አመጣጥ ተከትሎ የስጋት ደረጃ እየቀነሰ እንደምገኝ የክልሉ ሪፓርት ያመላክታል፡፡

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ በሣምንቱ በመደበኛ ሁኔታ ከሚታዩ የእንስሳት በሽታ ውጪ በወረርሽኝ መልኩ የተከሰተ የእንስሳት በሽታ ክስተት አለመኖሩን ከክልሉ የተገኘው መረጃዎች ያመለክታል፡፡

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

የኮሮና ቫይረስ በሽታ (COVID-19) በክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጋቢት 21/2012ዓ.ም በበንሳ ወረዳ ጋማጮ ቀበሌ በ2 ሰዎች ላይ መገኘቱከተመዘገበበት ቀን አንስቶ በክልሉ በሁሉም ወረዳዎች እና የከተማ አስተዳደር እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት እስከ ሳምንቱ መጨረሻ ድረስ በጠቅላላ ምርመራ ከተደረገላቸዉ 99,927 ሰዎች ዉስጥ ቫይረሱ በደማቸዉ ስለመኖሩ የተረጋገጠ 12,901 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አገግመው የወጡ ህሙማን ብዛት 12,599 ሲሆን

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

እስካሁንበአጠቃላይ በበሽታው 246ሞት የተመዘገበ መሆኑን ከሲዳማ ክልል የማህበረሰብ ጤና እንስቲትዩት የተገኘዉ መረጃ ያሳያል፡፡

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በመካከለኛ ደረጃ ለምግብ እጥረት/አለመመጣጠን ለተጋለጡ ከ5 አመት ዕድሜ በታች ለሆኑ ሕፃናት፣አጥቢና ነፍሰ-ጡር እናቶች በመደበኛ በፕሮግራሙ በታቀፉ3 ወረዳዎችና በተጋላጭነት ደረጃ በትኩረት አንድ (Hotspot Priority1) ከተመደቡ 6 እንደዚሁም የተቀናጀ እናቶችና የህጻናት ህክምና አገልግሎት (IMAM) 3 ወረዳዎች በጠቅላላው በ12 ወረዳዎች ለሚያዝያ እና ለግንቦት ወር የሚያስፈልገው ለእናቶች የሚሆን አልሚ-ምግብ 4,788.7 ኩ/ል እና ለሕፃናት 1548.6 ኩ/ል በድምሩ 6,337.3 ኩ/ል ቀርቦ በሁሉም ፕሮግራም ወረዳዎች በስርጭት ላይ የገኛል፡፡

በምግብ እጥረት በሽታ ምክንያት ተመላላሽ ታካሚ (OTP) ሕጻናት የክልሉ ቁጥር በዚህ ሳምንት ከ231 ወደ 218 ዝቅ ያለ ቢሆንም ከባለፈዉ ሳምንት ጋር ሲነፃፀር በሰባት ወረዳዎች ከ1 እስከ 6 በቁጥር ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በሌላ በአዲስ መልኩ ወደ ተኝቶ ህክምና የገቡ ሕጻናት (SC) ጥቅል ቁጥር ከባለፈዉ ሳምንት ጋር ስነፃፀር ከ17 ወደ 20 ከፍያለ ሲሆን ቁጥሩ ከባለፈዉ ሳምንት ጋር ስነጻጸር በመጠነኛ ጭማር አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም የሕክምና ፕሮግራሞች (OTP እና SC) አዲስ የገቡ ሕጻናት ቁጥር ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር የተመላላሽ ታካሚ ቁጥር መጠነኛ ቅናሽ የታየባቸዉ ቢሆንም የተኙቶ ታካሚ ህፃናት ቁጥር ጭማር የሚያሳይ በመሆኑ ወረዳዎች በህፃናት አመጋገብ ሥርዓት/የሕፃናትአያያዝ/...ወ.ዘ.ተ እና የምቀርበዉን የሕፃናት ምግብ በምክረ ሀሳቡ መሠረት እንድጠቀሙ ማድረግ እንደምገባ እንጠቁማለን፡፡

**4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

የበልግ ዝናብ ተጠናክሮ ባለመምጣቱ የገፀ-ምድርና ከርስ-ምድር ውሃ አቅርቦት ማነስ ከውሃ ተቋማት ብልሽት ችግሮች ከበጋ ወራት መጠናከር ጋር ተጣምሮ በክልሉ ቆላማ ወረዳዎች የዉሃ አቅርቦት ችግር እንድባባስ መንስኤ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ የዉሃ መሠረተ ልማት ባልተዳረሰባቸዉ በቆላማ ወረዳዎች ህብረተሰቡ የመጠጥ ዉሃ ፍለጋ ረጅም ኪሎ ሜትር ከመሄዳቸዉም በላይ አንድ ጃርካን የመጠጥ ዉሃ ከ25-30 ብር ለመግዛት እየተገደዱ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በቆላማ ወረዳዎች በጊዜያዊነትና በዘላቂነት የዉሃ ችግር ለመፍታት መረባረብ እንደምገባ እንጠቁማለን፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት
# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በ2013 በልግ ቅድመ-ምርት ግምገማ መሠረት የምግብ ክፍተት እንደሚገጥማቸው ለተለዩ 624,088 ወገኖች እና ለ18,470 ተፈናቃዮች በሙሉ ፓኬጅ ባይሆንም የ4ኛ ዙር የእለት እርዳታ በዓይነት ቀርቦ የተሰራጨ ሲሆን 5ተኛ ዙር (ብላቴ ዙሪ፣ቦርቻ፣ዳራ፣ዳሌ፣ ሸበዲኖ እና ሀዋሳ ዙሪያ) ወረዳዎች ብቻ ሙሉ በሙሉ ቀርቦ ስሰራጭ (ቦና ዙሪያ፤ሎካ አባያ፤አለታ-ጩኮ እና አለታ ወንዶ) ወረዳዎች በከፍል የቀረበ ሲሆን ለቀሪ ወረዳዎች ባለመቅረቡ ተጠብቆ ይገኛል። ለተፈናቃይ ወገኖች የሁሉም ወረዳ ቀርቦ ተሠራጭቷል። የ2013/14 መኸር ምርት ግምገማ መሠረት 454,774 ምግብ ክፍተት ላለባቸዉ እና 67,874 ተፈናቃይ በድምሩ 522,648 ተጠቃሚዎች 1ኛ ዙር የዕለት ዕርዳታ ተጠይቆ ይገኛል።

**6. ሌሎች አደጋዎች**

**6.1. ከባድ ዝናብ እና የበረዶ አደጋን በተመለከተ**

በክልሉ በሁላና ጭሮኔ ወረዳዎች በጣለዉ ድንገተኛ ዝናብ በተከሰተዉ ጎርፍበሰብል ማሳ ላይ ጉዳት ሲደርስ በቡራና ቦና ዙሪያና ወረዳ ንፋስ ቀላቅሎ በጣለዉ በረዶ በወቅታዊና ቋሚ ሰብል ላይ ጉዳት መድረሱን የክልሉ ሪፖርት ያሳያል።

**6.2. አዉሎ ንፋስ**

በክልሉ በጫቤ ጋንበልቶ ወረዳ በተከሰተዉ ከባድ ንፋስ አንድ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ወድሟል።

**7.የምግብ ሰብሎች እና የእንስሳት ገበያ አቅርቦትና ዋጋ ሁኔታ**

በሣምንቱ የምግብ እህልና የእንስሳት የገበያ አቅርቦት ሁኔታን ከካለፈዉ ሳምንት ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ሲሆን በዋጋ ደረጃ በዋና ዋና የምግብ እህሎች እና እንስሳት ላይ በአብዘኛዉ ጭማሪ መኖሩን እንዲሁም በአጠቃላይ ሲታይ የምግብ እህሎች እና እንስሳት የገበያ ዋጋ ካለፉት ዓመታት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የታየው ጭማሪ በዝቅተኛገቢ የምተዳደሩ የህብረተሰብ ክፍልን አቅም የሚፈታተን እንደሆነ መረጃ ያመለክታል።

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

### ሠንጠረዥ 2፦ ዝርዝር የገበያ መረጃን በተመለከተ

| ተቁ | ወረዳዎች | የገበያ ጊዜ | በቆሎ | ሠ/ጤፍ | ስንዴ | ባቄላ | ቦሎቄ | ቆጮ | ጫት | ቡና | በሬ | ላም | በግ | ፍየል | ዶሮ በአማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀዋሳ ዙሪያ | ባለፈው ሳምንት | 1900 | - | - | - | 4800 | 750 | - | - | 15000 | 9500 | 4400 | 2500 | 150 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2000 | | | | 5000 | 1450 | | | 17500 | 9500 | 6000 | 6500 | 375 |
| 2 | ወንዶ ገነት | ባለፈው ሳምንት | 2600 | 5000 | 4200 | 4500 | - | 1800 | 8000 | 16000 | 17000 | 15000 | 4200 | 4500 | 325 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2600 | 5000 | 4500 | 5000 | - | 2000 | 7000 | 20000 | 25000 | 19500 | 5000 | 5200 | 475 |
| 3 | ማልጋ | ባለፈው ሳምንት | 2500 | - | 4800 | 4070 | - | 1050 | 8000 | 16000 | 17000 | 13500 | 2700 | 2100 | 225 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2500 | - | 4450 | 4600 | - | 1500 | 4000 | 17000 | 18000 | 14000 | 2400 | 2500 | 290 |
| 4 | ሀዌላ | ባለፈው ሳምንት | 2500 | 4200 | 3000 | 4200 | 3000 | 1500 | 4000 | 17000 | 9000 | 7600 | 3200 | 3000 | 200 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2600 | 4200 | 3500 | 4200 | 3000 | 1500 | 4000 | 17000 | 9000 | 7500 | 3200 | 3000 | 230 |
| 5 | ጎርቼ | ባለፈው ሳምንት | 2400 | - | 4000 | 4300 | - | 900 | 6000 | 15000 | 15000 | 8000 | 2500 | 2300 | 200 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2400 | | 4000 | 4200 | | 900 | 5600 | 16000 | 16000 | 9000 | 2700 | 2500 | 240 |
| 6 | ሸበድኖ | ባለፈው ሳምንት | 2400 | 4800 | 3800 | 4100 | 4500 | 1700 | 4200 | 17000 | 9800 | 7900 | 3100 | 3300 | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2450 | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 7 | ቦርቻ | ባለፈው ሳምንት | 2000 | - | - | - | - | - | 4600 | 19000 | 15000 | 12500 | 3800 | 4000 | 200 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2000 | | | | 4000 | 2300 | 4600 | 19000 | 16500 | 13000 | 4200 | 4600 | 315 |
| 8 | ብላቴ ዙርያ | ባለፈው ሳምንት | 1900 | - | - | - | 3800 | 1200 | 3000 | 16000 | 17000 | 14000 | 2700 | 3000 | 250 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2000 | | | | 3500 | 1200 | 3200 | 16500 | 17000 | 15000 | 2800 | 3200 | 325 |
| 9 | ዳራራ | ባለፈው ሳምንት | 2100 | 4800 | - | - | 4000 | 1600 | 1600 | 20000 | 18000 | 14000 | 4000 | 4500 | 27 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2100 | 4800 | | | 4000 | 1600 | 6000 | 18000 | 20000 | 14000 | 4500 | 5000 | 375 |
| 10 | ሎካ አባያ | ባለፈው ሳምንት | 2600 | 4900 | - | - | 5000 | 1500 | 3400 | 20000 | 17000 | 13000 | 2800 | 3000 | 400 |
| | | በዚህ ሳምንት | -- | | | | 5500 | 1500 | 3200 | 20000 | 18000 | 15000 | 4000 | 4500 | 525 |
| 11 | ዳሌ | ባለፈው ሳምንት | 2600 | 5000 | 4000 | 5000 | 4200 | 1700 | 6000 | 17000 | 20000 | 11000 | 3900 | 4500 | 325 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2600 | 5000 | 4500 | 5000 | 3200 | 2500 | 6000 | 17000 | 20000 | 11000 | 3900 | 4500 | 295 |
| 12 | ወንሾ | ባለፈው ሳምንት | 2600 | - | 3500 | 4500 | 3800 | 1000 | 4300 | 18000 | 18000 | 15000 | 3400 | 3200 | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2600 | | 3600 | 4600 | 3300 | 1000 | 4700 | 18000 | 18500 | 16500 | 3600 | 3400 | 350 |
| 13 | አለታ ወንዶ | ባለፈው ሳምንት | 2800 | 4500 | 4000 | 4500 | 3200 | 2000 | 2500 | 18000 | 16500 | 8500 | 2800 | 3000 | 330 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2800 | 4700 | 4500 | 4600 | 3200 | 2000 | 2500 | 20000 | 17000 | 9000 | 2800 | 3000 | 350 |
| 14 | ዳራ | ባለፈው ሳምንት | 2700 | 4900 | 3800 | 4400 | 2800 | 1300 | 6500 | 16000 | 17000 | 14000 | 3000 | 3200 | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2700 | 4900 | 3400 | 2800 | 4400 | 1300 | 6500 | 16000 | 17000 | 14000 | 3000 | 3200 | 350 |
| 15 | ዳራአት ልቾ | ባለፈው ሳምንት | 2400 | 4500 | 3800 | 4500 | 3900 | 1000 | 8000 | 18000 | 17000 | 15000 | 3500 | 4000 | 280 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2400 | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 16 | አለታ ጩኮ | ባለፈው ሳምንት | 3000 | 4800 | 4500 | 5000 | 4000 | 950 | 5000 | 17000 | 15000 | 12000 | 2800 | 3000 | 250 |
| | | በዚህ ሳምንት | 3000 | 4800 | 4500 | 5000 | 4000 | 950 | 5000 | 17000 | 13000 | 11000 | 2800 | 3000 | 300 |

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

## (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

| ተቁ | ወረዳዎች | የገበያ ጊዜ | በቆሎ | ሠ/ ጤፍ | ስንዴ | ባቄላ | ቦሎቄ | ቆጮ | ጫት | ቡና | በሬ | ላም | በግ | ፍየል | ዶሮ በአማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ሁላ | ባለፈው ሳምንት | 3300 | 4700 | 4200 | 4800 | 4800 | 1600 | - | - | 18000 | 9500 | 4000 | - | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 18 | ጭሮኒ | ባለፈው ሳምንት | 2300 | - | 3200 | 3850 | 3850 | 1300 | - | - | 18000 | 10500 | 2400 | - | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 19 | ጠጢቻ | ባለፈው ሳምንት | 2600 | - | 2800 | 3400 | - | 1400 | - | - | - | - | 3400 | 2900 | 290 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2400 | | 2500 | 3400 | | 1500 | | | | | 3500 | 2900 | 320 |
| 20 | ቡርሳ | ባለፈው ሳምንት | - | - | 3000 | 3000 | 3000 | 1500 | - | - | 18000 | 10000 | 2400 | - | 200 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2600 | | 2600 | 4100 | | 1200 | | | 18000 | 10000 | 2600 | | 290 |
| 21 | ሻፋሞ | ባለፈው ሳምንት | 2800 | 4200 | 4200 | 5500 | - | 1800 | - | - | 15000 | 12000 | 1800 | - | 250 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 22 | አርቤ ጎና | ባለፈው ሳምንት | 2800 | - | 3600 | 4050 | - | 1700 | - | - | 20000 | 15000 | 3500 | 2200 | 350 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2700 | | 3500 | 4700 | | 1600 | | | 15000 | 14000 | 3400 | 3600 | 385 |
| 23 | ቦና ዙሪያ | ባለፈው ሳምንት | 3000 | 4500 | 3600 | 4350 | 2500 | 2150 | 2565 | | 18450 | 12460 | 2940 | 2860 | 350 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 24 | ቡራ | ባለፈው ሳምንት | 2800 | - | 3600 | 3600 | - | 1500 | - | | 15000 | 13000 | 2900 | 2600 | 260 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2500 | | 3600 | 3600 | | 1500 | | | 16000 | 14000 | 3900 | 2500 | 260 |
| 25 | በንሳ | ባለፈው ሳምንት | 3000 | 4050 | 3250 | 4700 | 3440 | 1420 | 3400 | | 18200 | 15500 | 3500 | 3700 | 280 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 26 | ጫቤ | ባለፈው ሳምንት | 2800 | 4500 | 3900 | 4400 | 3500 | 1100 | 3800 | | 18000 | 9500 | 2400 | 3900 | 325 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 27 | ሆኮ | ባለፈው ሳምንት | 2400 | - | - | - | 2600 | 1100 | 6000 | | 20000 | 16500 | 3800 | 4200 | 300 |
| | | በዚህ ሳምንት | 2000 | | 3800 | | | 1000 | | | 23000 | 18500 | 4500 | 6000 | 440 |
| 28 | አሮሬሳ | ባለፈው ሳምንት | 2700 | 4200 | 4000 | 4500 | - | 1800 | 4000 | | 12000 | 9000 | 3300 | 3500 | 280 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 29 | ዳኤላ | ባለፈው ሳምንት | - | - | - | 3300 | - | 650 | - | - | - | - | - | - | - |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 30 | ጭሬ | ባለፈው ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | 16000 | 12300 | 2700 | - | 280 |
| | | በዚህ ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| 31 | ሀዋሳ ከተማ | ባለፈው ሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | | - | - | - | - | - |
| | | በዚህ ሳምንት | | | | | | | | | | | | | |

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**በደቡብ ምዕ/ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል**

**1. የዝናብ ሁኔታ**

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ በክልሉ ሁሉም ዞኖች መረጃ ማግነት የተቻለ ሲሆን መረጃ ከተወሰደባቸው ዞኖች 2 ዞኖች /ሸካ እና ቤንች ሸኮ/ ዝናብ አግኝተዋልል ። የዝናቡ መጠን ዝቅተኛ ሲሆን ሥርጭቱ ሁሉንም ቀበሌዎች ያዳረሰ እንደነበር እና የተቀሩት ዞኖች ዝናብ አለመኖሩን የክልሉ መረጃ ያመለክታል።

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1.የበጋ መስኖ እና የበልግ እርሻ ስራ እንቅስቃሴን በተመለከተ**

በክልሉ ለበልግ እርሻ 287414.5 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ እስከዚህ ሳምንት በድምሩ 281676 ሄ/ር ታርሶ ለዘር ዝግጁ የሆነ ሲሆን *እስከ ሳምንቱ መጨረሻ 234986* ሄ/ር በዘር ተሸፍኗል።

በበጋ መስኖ ስንዴ *40021.66* ሄ/ር ታቀደ ሲሆን *15024.5* ሄ/ር ታርሶ *7633.25* ሄ/ር በዘር ተሸፍኖ ምርቱ እየተሰበሰበ መሆኑን የክልሉ መረጃ መለክታል።

**2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ቀደም ብሎ የተዘሩ እና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የአገዳ ሰብሎች ላይ ፎል አርሚ ወርም ክስተት በስፋት የታዪ ሲሆን በባህላዊ እና በኬሚካል ለመከላከል ጥረት እየተደረገ መሆኑን የክልሉ መረጃ ያመለክታል።

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በሳምንቱ በክልሉ በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ጥሩ እርጥበት በመኖሩ ምክንያት የእንስሳት መኖ እና ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የታየበት ነበር በመሆኑም ሪፖርት በቀረበባቸው ዞኖች የእንስሳት ሰውነት አቋም ከመደበኛ ጋር ተቀራራቢ እና በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኝመሆኑን የክልሉ ሪፖርት ያመለክታል።

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ በሳምንቱ ውስጥ በወረርሽኝ መልክ የተከሰተ በሽታ አለመኖሩን የክልሉ እሪፖርት ያመለክታል።

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

በምዕራብ ኦሞ ዞን ሱርማ ወረዳ የወባ ክስተት ከፍ ብሎ የታየ ሲሆን የ 2 ሰው ሞት መከሰቱን ከክልሉ የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በ2013/14 ዓ/ም የመኸር እና በልግ ቅድመ-ምርት ግምገማ መሠረት የምግብ ክፍተት እንደሚገጥማቸው ለተለዩ ከፋ ዞን ተረጂዎች እንዲሁም ሸካ ዞን ተፈናቃዮች እስካሁን ድጋፍ አልገባላቸውም፡፡ በተጨማሪም በዳውሮ ዞን በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የምግብ ድጋፍ እየገባላቸው ስርጭትም እየተካሄደ ቢሆንም ክስተቱ ከፍ ያለ ጉዳት ባደረሰበት ዛባጋዞ ወረዳ ድጋፍ ከቀረበ 2ኛ ወር እየሞላው በመሆኑ ህብረተሰቡ ዳግም ለችግር እንዳይዳረግ ስጋት አለ፡፡

**4.3. የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የውሃ አገልግሎት ሽፋን ባልተዳረሰባቸው እና በተለያዩ ምክንያቶች የተቋማት ብልሽት ካጋጠማቸው አካባቢዎች በስተቀር የጎላ የውሃ እጥረት ችግር አልታየም፡፡

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በዳዉሮ ዞን በተከሰተዉ ድርቅ ምክንያት በሳምንቱ ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ ከክልሉ መንግትሥት ፣ከአከባቢዉ ህብረተሰብ እንዲሁም መንግስታዊ ተቋማት ድጋፍ ሰብአዊ ድጋፍ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት ከፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ስንዴ 6684ኩ/ልእና አልሚ468 ኩ/ል ቀርቦ የተሰራጨ ሲሆን ለትኩረት አንድ ወረዳዎች /ሎማና ድሳ / 980 ኩ/ል አልሚ ምግብ ቀርቦ ስርጭት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በድርቅ ለተጎዱ አከባቢዎች ከህብረተሰብ እና ከተለያዩ ተቋማት  ቦሎቀ 118.5ኩ/ል፣በቆሎ 759 ኩ/ል፣ ባቀላ 57.5 ኩ/ል፣ ሩዝ 145.5 ኩ/ል፣ ማሽላ28.5 ኩ/ል፣ አተር29ኩ/ል፣ስንዴዱቀት260.5ኩ/ል ፤እና  ዘይት 100 ሊትር ለተጎጅዎችቀርቦ ስርጭት ተደርጓል፡፡

**6. ሌሎች አደጋዎች**

**6.1 የግጭት አደጋ**

በሳምንቱ ውስጥ በምዕራብ ኦሞ እና ኮንታ አጎራባች ቀበሌዎች በተከሰተ ግጭት በኮንታ ዞን 2 ቀበሌዎች ላይ የሰው ሞት እና መፈናቀል እንዲሁም የንብረት ውድመት አደጋ አጋጥሟል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

በዚሁ መሰረት-፡ የሞተ ሰው ብዛት 2 /ሁለት/፣ የአካል ጉዳት 3 ሰዎች በጽኑ ቆስለቀው ሆስፒታል ሲገቡ ከንብረት ውደመት ጋር በተያያዘ የ70 አባዎራዎች ቤት ሲዘረፍ የተፈናቀለ ሰው በሚመለከት አባዎራ 157 እማዎራ 11 በድምሩ 168 የቤተሰብ ኃላፊዎች እንዲሁም 390 ወንድ 432 ሴት በድምሩ 822 ቤተሰቦች ተፈናቅለዋል፡፡

## 7. የገበያ ሁኔታ

### 7.1 የምግብ ሰብሎች/የእንስሳት ገበያ አቅርቦትና ዋጋ ሁኔታ

በሣምንቱ  የዋና ዋና ሰብሎች እና እንስሳት እንስሳት ገበያ ዋጋ ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር የሰብል ዋጋ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን የቁም እንስሳት ዋጋ  ከባለፈዉ ሣምንት ጋር ሲነጻጸር ተቀራራቢ ነበር፡፡

| ዞኖች/ልዩወረዳዎች | የገበያጊዜ | ሠ/ጤፍ | ስንዴ | በቆሎ | ሩዝ | ባቀላ | አተር | ማሽላ | ቦሎቄ | ቅ/ቡና | በሬ | ላም | በግ | ፍዬል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቤንችሸኮ | ባለፈውሳምንት | 4800 | 3700 | 2300 | 4300 | 3900 | 4200 | 2200 | 2600 | 22000 | 23000 | 18000 | 5000 | 4500 |
| | በዚህሳምንት | 4800 | 3700 | 2300 | 4300 | 4000 | 4200 | 2200 | 2600 | 22000 | 23000 | 18000 | 5000 | 4500 |
| ከፋ | ባለፈውሳምንት | 4341 | 3739 | 2283 | 4100 | 3895 | 3917 | 2231 | 3448 | 16250 | 22806 | 14740 | 4,625 | 3,694 |
| | በዚህሳምንት | 4359 | 3679 | 2136 | 4081 | 3947 | 4128 | 2201 | 2865 | 16364 | 22382 | 15282 | 4723 | 3632 |
| ኮንታ | ባለፈውሳምንት | 4,500 | 3,600 | 2,400 | - | 3,600 | 3,600 | 3,300 | 3,600 | 15,300 | 26000 | 13,500 | 4,500 | 4,200 |
| | በዚህሳምንት | 4,600 | 3,600 | 2400 | - | 3000 | 3,300 | 2880 | 3,600 | 22240 | 22,000 | 13,100 | 4,450 | 3,900 |
| ዳዉሮ | ባለፈውሳምንት | 4,631 | 3,936 | 2,748 | - | 3,614 | 4,267 | 2,578 | 3,099 | 21,785 | 20,428 | 15,785 | 5,100 | 4,728 |
| | በዚህሳምንት | 4733 | 3761 | 2775 | - | 3918 | 4405 | 2812 | 3140 | 22037 | 22622 | 16922 | 5155 | 5000 |
| ሸካ | ባለፈውሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | |
| | በዚህሳምንት | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ምዕራብኦሞ | ባለፈውሳምንት | 4300 | 3500 | 2200 | - | 3000 | 3000 | 2100 | 2200 | 24000 | 24000 | 12000 | 2800 | 2600 |
| | በዚህሳምንት | 4300 | 3500 | 1800 | - | 3000 | 3000 | 1800 | 1800 | 20000 | 20000 | 12500 | 3600 | 3200 |

## ኦሮሚያ ክልል

### 1. የዝናብ ሁኔታ

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ኢሉ አባቦር ዞን 12 ወረዳዎች፣ ጅማ 20፣ ባሌ 1፣ ምስራቅ ባሌ 6፣ ቡኖበ ደሌ 9፣ ምስራቅ ወለጋ 17፣ ምእራብ

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

ሀረርጌ 1 ወረዳዎች እና ምእራብ ሸዋ 6 ወረዳዎች ከዝቅተኛ እስከ መከለኛ መጠን ያለው እና ሁሉንም አካባቢዎች ያላደረሰ ዝናብ የዘነበ ሲሆን በሌሎች የክልሉ ዞኖች እና ወረዳዎች ላይ አለመዝነቡን ከክልሉ የደረሰን መረጃ ያሳያል፡፡

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1 የበልግ ሰብሎች እድገት ደረጃ በተመለከተ**

በክልሉ የሚገኙ አብዛኛዉ ዞኖች እና ወረዳዎች የበልግ ሰብሎች በእድገት ደረጃ ላይ መሆናቸውን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

| ዞን | የታቀደ | የታረሰ | የተዘራ | የዘር አፈፃፀም ከታረሰዉ መሬት |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብ ጉጂ | 170153 | 172991 | 20771 | ------- |
| አርሲ | 150998 | 148455 | 32415 | -------- |
| ምዕራብ አርሲ | 57744.5 | 63298.5 | 45108 | |
| ምስራቅ ሐረርጌ | 332643 | 65258 | 47253 | |
| ምዕራብ ሐረርጌ | 276077 | 161034 | 27607 | ------- |
| ምስራቅ ሸዋ | 439120 | 105623 | | |
| ቦረና | 96156 | 65301 | 35541 | |
| ምስራቅ ባሌ | 109332 | 109332 | 109320 | |
| ጉጅ | 153664 | 151225 | 67371.5 | ------- |
| ባሌ | 225307 | 240338 | 240338 | ------- |
| ጅማ | 552713 | 470882 | 62773 | ------- |
| ድምር | 2563907.5 | 1846068 | 555297 | |

**2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ**

በሳምንቱ በክልሉ ፀረ-ሰብል ተባይ ክስተት አለመከሰቱን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ ምዕራብ ሀረርጌ በቆላማ አካባቢዎች እጥረት እና አርሲ ዞን እጥረት እጥረት መኖሩን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ የእንስሳት በሽታን በተመለከተ የደረሰ አደጋ የለም

**3.3 የእንስሳት የሰዉነት አቋምን በተመለከተ**

በክልሉ ቦረና ዞን፣ ጉጅ ዞን፣ ባሌ ዞን፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ እና ምስራቅ ባሌ ዞን ቆላማ አካባቢዎች የእንስሳት የሰዉነት አቋም መቀነሱን የክልሉ መረጃ ያመለክታል።

**4. የሰው ጤና ሁኔታ**

**4.1. የበሽታ ሁኔታ**

በክልሉ በቦረና ዞን ኤልወዬ ወረዳ  ወባ 26 ተቅማጥ 14 ድሎ ወረዳ ወባ 17 ተልተሌ ወረዳ ወባ 13 ተቅማጥ 8 ሰዎች መያዛቸውን መረጃዉ ያመለክታል።

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በክልሉ በሳምንቱ ሥርዓተ-ምግብን በተመለከተ ከክልሉ የተገኘ መረጃ የለም።

**4.3 የሰው መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ በተከሰተዉ የዉሀ እጥረት ምክንያት በምዕራብ ሀረርጌ ዞን 5 ቦቴዎች፣ ምስራቅ ሸዋ 4 ቦቴዎች፣ አርሲ ዞን 7 ቦቴዎች፣ ምእራብ አርሲ ዞን 6 ቦቴዎች፣ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን 13 ቦቴዎች፣ ምዕራብ ጉጅ ዞን 10 ቦቴዎች፣ ምስራቅ ባሌ ዞን 8 ቦቴዎች፣ ቦረና ዞን 3 ቦቴዎች እና ጉጂ ዞን 5 ቦቴዎች እንዲሁም ባሌ ዞን 7 ቦቴዎች ስራ ላይ ናቸው።

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

የ5ኛ ዙር እርዳታ ተሰራጭቶል።

**6. ሌሎች አደጋዎች**

**6.1 የእሳት አደጋ ክስተት**

በክልሉ በባሌ ዞን በድክስ ወረዳ በተከሰተው የእሳት አደጋ ምክንያት 1 ሳር ቤት እና 5 ቆርቆሮ ቤቶች ተቃጥሎ ግምቱ 645000 ብር የሆነ የ6 አባወራ ተጎጅ ሲሆኑ እዲሁም በሐጦሳ ወረዳ 1ሳር ቤት ግምቱ 52000 ብር የሆነ 1 አባወራ ተጎጅ መሆኑን የክልሉ መረጃ ያመለክታል።

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

## 7. የገበያ ሁኔታ

### 7.1. የእህል አቅርቦት እና የዋጋ ሁኔታ

በሳምንቱ ዋጋን በተመለከተ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን የአቅርቦት ችግር የሌለ ሲሆን ዋጋን በተመለከተ በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር ተመላክቶል።

### 7.2 የእንስሳት አቅርቦት እና የዋጋ ሁኔታ

በሳምንቱ ዋጋን በተመለከተ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን አቅርቦት በቂ ሲሆን ዋጋን በተመለከተ በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር ተመላክቶል።

**ሠንጠረዥ 1፡ ዝርዝር የእህልና የእንስሳት ዋጋ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

| ተቁ | ዞን | ጤፍ | ስንዴ | በቆሎ | ማሽላ | በሬ | ላም | በግ | ፍየል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቦራና | 6000 | 3500 | 3200 | ---- | 6100 | 2600 | 950 | 2620 |
| 2 | ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ | 3935 | 2485 | 1855 | 1155 | 14280 | 11125 | 2420 | 2315 |
| 3 | ጉጅ | 4820 | 3600 | 2710 | ------- | 8720 | 4200 | 1000 | 1180 |
| 4 | ባሌ | 4075 | 3225 | 2466 | 2550 | 22000 | 15125 | 2087 | 2188 |
| 5 | ምእራብ ጉጅ | 5300 | 4100 | 3500 | ------- | 9070 | 6050 | 2000 | 2600 |
| 6 | ቄለም ወለጋ | 5007 | 1875 | ------ | 1670 | 19050 | 16150 | 3900 | 3200 |
| 7 | ምስራቅ ሸዋ | 4300 | 3114 | 2380 | 3400 | 22000 | 18265 | 3900 | 3550 |
| 8 | ምስራቅ ባሌ | 5340 | 3150 | 2680 | 2800 | 10000 | 7680 | 1000 | 1420 |
| 9 | ደቡብ ምእራብ ሸዋ | 4050 | 3015 | 2410 | 3000 | 22015 | 13830 | 3360 | 3155 |
| 10 | አርሲ | 4822 | 3412 | 2988 | 3222 | 24560 | 12372 | 2870 | 2490 |
| 11 | ምስራቅ ሐረርጌ | 5490 | 3595 | 2700 | 3240 | 17500 | 10100 | 1750 | 1950 |
| 12 | ምስራቅ ወለጋ | 4087 | 2775 | 1909 | 2033 | 17836 | 12915 | 2469 | 2199 |
| 13 | ምእራብ ሸዋ | 4150 | 3110 | 2466 | 2428 | 20428 | 14422 | 2649 | 2449 |
| 14 | ምእራብ ወለጋ | 4862 | 3650 | 1988 | 2093 | 22200 | 14804 | 3886 | 3353 |
| 15 | ምእራብ አርሲ | 4614 | 3230 | 2600 | 3808 | 16983 | 12841 | 2212 | 2082 |
| 16 | ሰሜን ሸዋ | 4238 | 3541 | 2596 | 2984 | 30869 | 17808 | 3198 | 2861 |
| 17 | ቡኖ በደሌ | 4248 | 3181 | 2142 | 2390 | 20568 | 11812 | 3418 | 3328 |
| 18 | ኢሉ አባቦር | 4517 | 4066 | 2019 | 2525 | 28711 | 20337 | 6628 | 4225 |
| 19 | ጅማ | 4688 | 3648 | 2450 | 2818 | 22717 | 14084 | 4280 | 3640 |
| 20 | ምእራብ ሐረርጌ | 5180 | 3598 | 2900 | 3400 | 14967 | 9193 | 1613 | 1800 |

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

## አማራ ክልል

### 1. የዝናብ ሁኔታ

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በ7 ወረዳዎች፣ በምስ/ጎጃም ዞን በ4 ወረዳዎች እና በምዕ/ጎጃም ዞን በ3 ወረዳዎች በከፊል ዝናብ የዘነበ ሲሆን ለእንስሳት መኖ እና የመጠጥ ዉሃ ጉልህ አተዋፆ ይኖረዋል፡፡ በአዊ፣ በዋግኽምራ እና በሰ/ጎንደር ዞኖች በሁሉም ወረዳዎች እና በምዕ/ጎንደር ዞን በአንድ ወረዳ በሳምንቱ መረጃ አልተገኘም፡፡

### 2. የሰብል ሁኔታ

#### 2.1 የበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ

በ2014/15 ምርት ዘመን በበልግ ይለማል ተብሎ ከታቀደዉ 207,578 ሄ/ር መሬት ዉስጥ 194,418 ሄ/ር የታረሰ ሲሆን በሰ/ወሎ፣ በሰ/ሸዋ እና በደ/ወሎ ዞኖች 132,745 ሄ/ር መሬት ተዘርቷል፡፡ በ2014/15 ምርት ዘመን በመኸር ይለማል ተብሎ ከታቀደዉ 4,867,603 ሄ/ር መሬት ዉስጥ 2,334,191 ሄ/ር መሬት ታርሷል፡፡ 43,734 ሄ/ር መሬት ድንች እና ማሽላ ተዘርቷል፡፡ የሰብል የእድገት ደረጃ በደ/ወሎ ዞን በወረባቦ፣ በቃሉ፣ በመ/ሳይንት እና በአምባስል እና በሰ/ወሎ ዞን በዋድላ እና በግዳን ወረዳዎች በዝናብ እጥረት ምክንያት የበለግ ሰብል በመድረቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን በሌሎች ወረዳዎች ዝቅተኛ አቋም አለዉ፡፡

#### 2.2. የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ

በክልሉ ስለ ፀረ-ሰብል ክስተት በተመለከተ አዲስ የደረሰን መረጃ የለም፡፡

### 2. የእንስሳት ግጦሽ/መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ

በክልሉ በደ/ወሎ ዞን በደላንታ፣ በተንታ፣ በወረባቦ፣ በደ/ዙሪያ፣ በለገሂዳ፣ በአርጎባ፣ በለጋምቦ እና በመ/ሳይንት ወረዳዎች እና በሰ/ወሎ ዞን በሀብሩ፣ በራያቆቦ፣ በአንጎት እና በጉባላፍቶ ወረዳዎች በቆላማ ቀበሌዎች የመኖ እና የዉሃ እጥረት የታየ ሲሆን፤ በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች የእንስሳት መኖና መጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ ነው፡፡

#### 3.1. የእንስሳት የሰውነት አቋም ሁኔታ

በክልሉ በሰሜን ወሎ እና በደ/ወሎ ዞኖች የመኖ እና የእስሳት መጠጥ ዉሃ እጥረት ባለባቸዉ ወረዳዎች የአቋም መቀነስ የታየ ሲሆን በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች መካከለኛ እና ጥሩ የእንስሳት አቋም አለ፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

## (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

### 3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ

በክልሉ የእንስሳት በሽታን በተመለከተ የደረሰን ሪፖርት የለም ፡፡

### 3.3 የእንስሳት የሰውነት አቋም በተመለከተ

በሰ/ወሎ እና በደ/ወሎ ዞኖች የመኖ እና የእስሳት መጠጥ ዉሃ እጥረት ባለባቸዉ ወረዳዎች የአቋም መቀነስ የታየ ሲሆን በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች መካከለኛ እና ጥሩ የእንስሳት አቋም አለ፡፡

## 4. ሰዉ ጤና ሁኔታ

### 4.1 የበሽታ ሁኔታ

በክልሉ የሰው የጤና ሁኔታን በተመለከተ የተገኘ መረጃ የለም፡፡

### 4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ

በክልሉ ስርዓተ-ምግብን በተመለከተ የደረሰን አዲስ መረጃ የለም፡፡

### 4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተመለከተ

በክልሉ በቀወት፣ በእንሳሮ፣ በምንጃር እና በበረኸት ወረዳዎች የመጠጥ ዉሃ እጥርት የታየ መሁኑን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

| ተ.ቁ | ወረዳ | ቀበሌ | የተሰራጨ ዉሃ በሊትር | የተጠቃሚ ሰዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እንሳሮ | ደንቢ | 57,000 | 3,095 |
| | | ይድኖ | 38,000 | 4,842 |
| 2 | መርሃቤቴ | ጎረንዳ ማሪያም | 66,000 | |

## 5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ

በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች ለሚገኙ 11,641,554 የዕለት ምግብ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በአደጋ ስጋት አመራር፣ በአለም የምግብ ፕሮግራምና በJEOP በኩል እየቀረበ ሲሆን በአምስተኛ ዙር ከተጠየቀው ድጋፍ እስካሁን 83% ቀርቦ እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

በአደጋ ስጋት ስራ አመራር እየቀረበ ያለው የ5ኛ ዙር ድጋፍ አለመጠናቀቅና መጓጓዝ ማቅም ይታያል፡፡

## 6. ሌሎች አደጋዎች

በሳምንቱ በክልሉ የተከሰተ አደጋ የለም፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

## 7. የገበያ ሁኔታ

### 7.1 የእህል አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ

በደ/ወሎ ዞን በወረባቦ፣ በአርጎባ፣ በጀማ፣ በወግዲ እና በአምባሰል ወረዳዎች እና በሰ/ወሎ ዞን በሁሉም ወረዳዎች ቅናሽ የታየ ሲሆን በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ካለፈዉ ሳምንት ጋር ተመሳሳይ የእህል አቅርቦት ታይቷል፡፡ የዕህል አቅርቦትን በተመለከተ በደ/ወሎ እና በሰ/ወሎ ዞኖች በሁሉም ወረዳዎች ጭማሪ የታየ ሲሆን በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ካለፈዉ ሳምንት ጋር ተመሳሳይ የእንሳሳት አቅርቦት ታይቷል፡፡

### 7.2 የእንስሳት አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ

በሰ/ሸዋ ዞን በአተር እና በምስር፣ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በበቆሎ እና በምዕ/ጎጃም ዞን በአተር ላይ ጭማሪ የታየ ሲሆን በደ/ጎንደር ዞን በምስር ላይ መጠነኛ ቅናሽ ታይቷል፡፡ የእንስሳት አቅርቦትን በተመለከተ በሰ/ወሎ ዞን በላም፣ በምዕ/ጎጃም ዞን በበሬ እና በምስ/ጎጀም እና በሰ/ሸዋ ዞኖች በበሬ እና ላም ላይ ጭማሪ የታየ ሲሆን በደ/ወሎ ዞን በላም፣ በሰ/ወሎ ዞን በበሬ እና በደ/ጎንደር ዞን በበሬ እና ላም ላይ ቅናሽ ታይቷል፡፡

### ሰንጠረዥ 2፡- ዝርዝር የገበያ መረጃን በተመለከተ

| የእህል እና የእንስሳት ዋጋ | ሰሜን ሸዋ (1) | | ኦሮሞ (2) | | ደቡብ ወሎ (3) | | ሰሜን ወሎ (4) | | ዋግ ኽምራ (5) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የእህል አይነት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት |
| ጤፍ | 4206 | 4245 | 4445 | 4415 | 4445 | 4445 | መ.የለም | 4581 | መ.የለም | መ.የለም |
| ገብስ | 3303 | 3281 | 4300 | 4516 | 3469 | 3508 | መ.የለም | 3615 | መ.የለም | መ.የለም |
| ማሽላ | 2768 | 2914 | 2912 | 2987 | 2886 | 2884 | መ.የለም | 3133 | መ.የለም | መ.የለም |
| ስንዴ | 3181 | 3310 | 3200 | 3350 | 3103 | 3074 | መ.የለም | 3406 | መ.የለም | መ.የለም |
| በቆሎ | 2515 | 2442 | 2541 | 2530 | 2555 | 2555 | መ.የለም | 2874 | መ.የለም | መ.የለም |
| ባቄላ | 3908 | 3986 | 4594 | 4550 | 3947 | 3926 | መ.የለም | 4521 | መ.የለም | መ.የለም |
| አተር | 4303 | 4146 | 4873 | 4750 | 4515 | 4622 | መ.የለም | 4835 | መ.የለም | መ.የለም |
| ሽንብራ | 4300 | 4444 | 4427 | 4475 | 4063 | 4078 | መ.የለም | 4708 | መ.የለም | መ.የለም |
| ምስር | 8859 | 8923 | 11070 | 11070 | 9306 | 9328 | መ.የለም | 8523 | መ.የለም | መ.የለም |
| የእንስሳት አይነት | | | | | | | | | | |
| በሬ | 25615 | 27131 | 25380 | 25476 | 21175 | 22675 | መ.የለም | 17136 | መ.የለም | መ.የለም |
| ላም | 16159 | 17850 | 14882 | 14885 | 14750 | 14852 | መ.የለም | 13473 | መ.የለም | መ.የለም |

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በግ | 2688 | 2977 | 2889 | 2889 | 2620 | 2922 | መ.የለም | 2263 | መ.የለም | መ.የለም |
| ፍየል | 2753 | 2901 | 3552 | 3553 | 3012 | 3252 | መ.የለም | 2466 | መ.የለም | መ.የለም |
| ደሮ | 402 | 316 | 347 | 347 | 303 | 484 | መ.የለም | 239 | መ.የለም | መ.የለም |

| የእህል እና የእንስሳ ት ዋጋ | ደቡብ ጎንደር (6) | | ሰ/ጎንደር (7) | | ማዕ/ጎንደር (8) | | ምዕ/ጎንደር (9) | | ምስ/ ጎጃም (10) | | ምዕ/ጎጃም (11) | | አዊ (12) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈዉ ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈው ሳምንት | በዚህ ሳምንት | ያለፈዉ ሳምንት | በዚህ ሳምንት |
| ጤፍ | 3842 | 3949 | መ.የለም | መ.የለም | 3786 | 3700 | 4100 | 4150 | 3928 | 3959 | 4100 | 4100 | 4211 | 4272 |
| ገብስ | 2800 | 2815 | መ.የለም | መ.የለም | 2800 | 2720 | | | 3234 | 3263 | 3100 | 3200 | 2971 | 3114 |
| ማሽላ | 2354 | 2386 | መ.የለም | መ.የለም | 2516 | 2516 | 2466 | 2500 | 2668 | 2618 | | | | |
| ስንዴ | 3084 | 3097 | መ.የለም | መ.የለም | 2911 | 2820 | 5500 | 5500 | 3121 | 3053 | 3100 | 3150 | 3137 | 3331 |
| በቆሎ | 2100 | 2174 | መ.የለም | መ.የለም | 2168 | 2168 | 2300 | 2325 | 2353 | 2226 | 2100 | 2175 | 2183 | 2172 |
| ባቄላ | 3895 | 3761 | መ.የለም | መ.የለም | 3983 | 4100 | 5266 | 5266 | 3976 | 3976 | 4100 | 4200 | 4693 | 4668 |
| አተር | 4200 | 4276 | መ.የለም | መ.የለም | 4500 | 4650 | 6750 | 6500 | 4742 | 4807 | 4700 | 4750 | 4977 | 5075 |
| ሽንብራ | 4118 | 4120 | መ.የለም | መ.የለም | 4311 | 4411 | 6333 | 6333 | 4687 | 4642 | 4400 | 4500 | | |
| ምስር | 6245 | 6493 | መ.የለም | መ.የለም | 7800 | 7800 | 11333 | 11300 | 7056 | 7840 | | | | |
| የእንስሳ ት አይነት | | | | | | | | | | | | | | |
| በሬ | 16885 | 16892 | መ.የለም | መ.የለም | 19866 | 21500 | 22366 | 22777 | 24553 | 24652 | 24000 | 24500 | 24222 | 25888 |
| ላም | 14181 | 14473 | መ.የለም | መ.የለም | 15216 | 16500 | 16400 | 17100 | 14815 | 14800 | 17000 | 17500 | 18035 | 17555 |
| በግ | 2298 | 2298 | መ.የለም | መ.የለም | 2318 | 2550 | 2166 | 2183 | 3136 | 3188 | 3800 | 3800 | 3977 | 4188 |
| ፍየል | 2158 | 2154 | መ.የለም | መ.የለም | 1983 | 2050 | 2153 | 2166 | 2653 | 2663 | 3200 | 3400 | 3911 | 3975 |
| ደሮ | 218 | 208 | መ.የለም | መ.የለም | 263 | 285 | 353 | 330 | 312 | 318 | 350 | 360 | 335 | 345 |

## ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል

### 1. የዝናብ ሁኔታ

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ በክልሉ ሥር ባሉ በሁሉም ወረዳዎች በሚባል ደረጃ የነበረው የአየር ሁኔታ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር መደበኛ ሲሆን የዝናብ ሁኔታን በተመለከተ በክልሉ አብዛኛው ወረዳዎች ላይ መካከለኛ የዝናብ ስርጭት የነበረና በሽፋን በኩል ግን ሁሉንም ወረዳዎች ያዳረሰ ብሆንም በተወሰኑ ወረዳዎች በመጠን አነስተኛ አልፎ አልፎ እየዘነበ ነው፡፡በተለይ በክልሉ ባሉ ጠረፋማ አከባቢዎች ወረዳዎች ላይ ማለትም ኩርሙክ፣ ሽርቆሌ፣ መንጌ እና ጉባ የዝናቡ ስርጭት አለመኖሩን ለማስተዋል ተችሏል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1 የሰብሎች እድገት ደረጃን በተመለከተ**

በክልሉ በምርት ዘመኑ የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ በክልሉ አንፃራዊ ሠላም ባለባቸው ዞንና፣ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ላይ የማሳ ፅዳትና ሌለዎች ሥራዎች በማከናወን ላይ መሆናቸውን ከክልሉ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ**

በክልሉ በሳምንቱ የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተት አለመኖሩን ከክልሉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በአሁኑ ወቅት የክረምቱ ዝናብ ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ የእንስሳት መኖም ሆነ የመጠጥ መደበኛ ስለሆነ የተለየ ውሃ አቅርቦት ችግር የለም፡፡

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ የእንስሳት በሽታን በተመለከተ በመደበኛ ከሚከሰቱ በሽታዎች በስተቀር በወረርሽኝ ደረጃ የተከሰተ በሽታ የለም፡፡

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

በአጠቃላይ የሰው ጤና በተመለከተ በመደበኛነት ከሚከሰቱ በሽታዎች ውጪ በወርሽኝ መልክ የተከሰተ የሌለ መሆኑን ለማወቅ የተቻ ለሲሆን ከወቅቱ የዝናብ አጀማመር ጋር በተያያዘ እንደወባ ያሉ በሽታዎች ሊከሰቱ ስሚችሉ ከወዲሁ ለመከላከል በየሳምንቱ መረጃ በመለዋወጥ የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች ላይ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በሳምንቱ ሥርዓተ-ምግብን በተመለከተ ከክልሉ የተገኘ መረጃ የለም፡፡

**4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ በሚገኙ አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ላይ ያለው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተመለከተ ከዝናብ ሥርጭት መሻሻል ጋር በተያያዘ የውሃ አቅርቦት በአካባቢያቸው በቀላሉ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት
# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ ምግብ ነክ የሆኑና ምግብ ነክ ያልሆኑ የ5ኛ ዙር የዕለት እርዳታዎች በተመለከተ እየተጓጓዘ ሲሆን፤ የ6ኛ ዙር የእለት እርዳታ አስመልክቶ የተጠየቀ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ምንም አይነት ምላሽ አልተሰጠ፡፡

**6. ሌሎች አደጋዎች**

በሳምንቱ አዲስ የተከሰተ አደጋ የለም፡፡

7. **የገበያ ሁኔታ**

በዚህ ሳምንት የምግብ እህልና የቤት እንስሳት የገበያ አቅርቦት ሁኔታዎችን በተመለከተ በዋና ዋና የምግብ እህሎች እና በቤት እንስሳቶች እንዲሁም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

| *የሰብል ዓይነት* | *አሶሳዞን* | *መተከልዞን* | *ካማሽ* | *የእንሰሳት ዓይነት* | *አሶሳን* | *መተከልን* | *ከማሽ* |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በቆሎ | 2650 | 2450 | 2850 | **በሬ** | 65000 | 48600 | 49000 |
| ማሽላ | 2700 | 2500 | 2950 | **ላም** | 49000 | 35500 | 37000 |
| ጤፍ | 5400 | 4700 | 4900 | **በግ** | 6500 | 5500 | 5600 |
| ዳጉሳ | 2800 | 2400 | 3200 | **ፍየል** | 4500 | 42000 | 4000 |
| ቦሎቄ | | | | **ዶሮ** | 1200 | 800 | 750 |
| ሎውዝ | | | | | | | |

## ጋምቤላ ክልል

**1. የዝናብ ሁኔታ**

በክልሉ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ በክልሉ በሚገኙ 13 ወረዳዎች መካከል በ11 ወረዳዎች ማለት መጃንግ ዞን ጎደሬና መንገሽ፣ አኙዋ ዞን አበቦና ጎግ፣ ጋምቤላ ዙሪያ ጆርና ዲማ፣ በንዌር ዞን ላሬና መኳይ፣ ጂካዎ፣ ኢታንግ፣ ልዩና ጋምቤላ ከተማ በመጠን ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ መዝነቡን የክልሉ ሪፖርት ያመለክታል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

## 2. የሰብል ሁኔታ

### 2.1 የሰብል እድገት ደረጃን በተመለከተ

በክልሉ መጃንግ ዞን ጎደሬና መንግሽ፣ አኝዋ ዞን ዲማ ወረዳ የቦቆሎና ሰሊጥ ሰብል አረም የተጀመረ ሲሆን በሌሎች አኝዋ ዞን አበቦና ጎግ፣ ጋምቤላ ዙሪያ ጆርና፣ በንዌር ዞን ላሬ፣ መኳይ፣ ጂካዎ፣ ኢታንግ ልዩና ጋምቤላ ከተማ የቦቆሎ ዘር ሥራና የማሳ ዝግጅት ላይ መሆናቸዉን ከክልሉ የደረሰን መረጃ ይገልጻል፡፡

### 2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ

በሳምንቱ የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን አለመኖሩን የደረሰን መረጃ ይገልጻል፡፡

## 3. የእንስሳት ሁኔታ

### 3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ

በክልሉ በሳምንቱ የእንስሳት መኖና የውሃ አቅርቦት ችግር የለም፡፡

### 3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ

በክልሉ በወረርሽኝ ደረጀ የተከሰተ የእንስሳት በሽታ የለም፡፡

## 4. የሰው ጤና

### 4.1 የበሽታ ሁኔታ

በክልሉ የሰው ጤና በተመለከተ የደረሰን መረጃ የለም ፡፡

### 4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ

በክልሉ ስርዓተ-ምግብን በተመለከተ የደረሰን አዲስ መረጃ የለም፡፡

### 4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ

በክልሉ በሳምንቱ የመጠጥ ውሃ እጥረት አለመኖሩን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

## 5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ

የ2013 ተረጂ በፀደቀው መሰረት የምግብ ክፍተት ላለባቸው ለ60,362 የአምስተኛ ዙር እርዳታ እየቀረበ ይገኛል፡፡

## 6. ሌሎች አደጋዎች

በሳምንቱ በመስተዳድሩ የተከሰተ አደጋ የለም፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**7. የገበያ ሁኔታ**

**7.1 የእህል እና የእንስሳት አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ**

የእህል አቅርቦት በተመለከተ በዋጋ ቁጥጥር ምክንያት የምግብ እህል ነጋዴዎች እያቀረቡ አይደለም፡፡ ከዋጋ አንፃር ግን የእህልም ሆነ የእንስሳት ጭማሪ አሳይቷል፡፡

| ተቁ | ዓይነት | መለኪያ | የአንዱ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ቦቆሎ | | 4200 |
| 2 | ማሽላ | | 4150 |
| 3 | በሬ | | 28500 |
| 4 | በግ | | 7800 |
| 5 | ፍየል | | 6700 |
| 6 | አውራዶሮ | | 650 |

## ድሬዳዋ መስተዳድር

**1. የዝናብ ሁኔታ**

በመስተዳድሩ ከግንቦት 02/2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም ባለዉ ባለዉ ጊዜ ለ3 ቀናት ዝናብ የዘነበ መሆኑን ከመስተዳድሩ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1 የሰብል እድገት ደረጃን በተመለከተ**

በመስተዳደሩ የሰብል ሁኔታን በገኘነው መረጃ መሰረት የመኸር እርሻ የታቀደው 11,964 ሲሆን የታረሰውና የተዘራው10,106 ነው፡፡

**2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ**

በሳምንቱ የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ ከመስተዳደሩ የደረሰን መረጃ የለም፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በመስተዳደሩ ግጦሽ/መኖና እጥረት አለ፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በሣምንቱ በአብዛኛው የመስተዳድሩ አካባቢዎች በመደበኛ ሁኔታ ከሚታዩ የእንስሳት በሽታዎች ውጭ በወረርሽኝ መልክ የተከሰተ የእንስሳት በሽታ አለመኖሩን የመስተዳድሩ መረጃ ያመለክታል፡፡

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

የሰው የጤና ሁኔታን በተመለከተ ከመስተዳድሩ የተገኘው መረጃ የለም፡፡

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በሳምንቱ የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ ከመስተደዳሩ የተገኘ መረጃ የለም፡፡

**4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በመስተዳድሩ የውሃ እጥረት ከመደበኛ ጋር ተቀራራቢ መሆኑን የመሰተዳደሩ መረጃው ያመለክታል፡፡

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በመስተዳድሩ 5[ተኛ] ዙር እርዳታ ተሰራጭቷል፡፡

**6. ሌሎች አደጋዎች**

በሳምንቱ በመስተዳድሩ የተከሰተ አደጋ የለም፡፡

**7. የገብያ ሁኔታ**

**7.1 የእህል አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ**

በሳምንቱ የዕህል ዋጋን በተመለከተ ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር የአቅርቦት እጥረት ባይኖርም ዋጋን በተመለከተ ከባለፈው ሳምት ጋረ ተመሳሳይ ነው፤ ለአብነት የጤፍ 5300 ብር፣ ማሽላ ከ4000 ብር፣ ስንዴ 4500 ብር እና በቆሎ 2500 ብር መሆኑን ከመስተዳድሩ የደረሰን መረጃ ያስረዳል፡፡

**7.2 የእንስሳት አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ**

በሳምንቱ የእንስሳት የገበያ ሁኔታ በተመለከተ ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ነው፣ ለአብነት በሬ 40000 ብር፣ ላም 25 000 ብር፣ በግ 4000 ብር እና ፍየል 4000 ብር መሸጡን የክልሉ መረጃ ያስረዳል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት
# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

***ሀረሪ ክልል***

**1. የዝናብ ሁኔታ**

በክልሉ ከሚያዚያ 18/2014 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 24/2014 ዓ.ም ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ምንም ዝናብ አለመዝነቡን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

**2. የሰብል ሁኔታ**

**2.1 የሰብል እድገት ደረጃን በተመለከተ**

በክልሉ የሰብል ሁኔታን በተመለከተ ተሰብስበዉ የገቡ ሲሆን በመስኖ የሚለሙ የጓሮ አትክልቶች ለምግብነት በመድረስ ደረጃ ላይ መሆናቸዉን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

**2.2 የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ**

በሳምንቱ የፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን አለመኖሩን የደረሰን መረጃ ይገልጻል፡፡

**3. የእንስሳት ሁኔታ**

**3.1 የእንስሳት ግጦሽ/መኖና ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ የእንስሳት መኖና የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በክልሉ አብዛኘው ወረዳ ላይ እጥረት መኖሩን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

**3.2 የእንስሳት በሽታን በተመለከተ**

በክልሉ የእንስሳት በሽታን በተመለከተ የተከሰተ የለም ፡፡

**4. የሰው ጤና**

**4.1 የበሽታ ሁኔታ**

በሳምንቱ በክልሉ የሰው የጤና ሁኔታን በተመለከተ ኮቪድ-19 በተመለከተ ከተመረመሩት 101 ሰዎች ዉስጥ በሽታው ያልተገኘ መሆኑን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

**4.2 የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታን በተመለከተ**

በክልሉ ስርዓተ-ምግብን በተመለከተ ተኝቶ ታካሚዎች 5 ሲሆኑ ተመላላሽ ታካሚዎች 28 መሆናቸዉን ከክልሉ የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

**4.3 የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተመለከተ በቂ በሚባል ደረጃ ላይ መሆኑን የክልሉ መረጃ ያመለክታል፡፡

# ከክልሎችና ዞኖች የተሰበሰበ ሳምንታዊ የአየርና የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ ሪፖርት

# (ከግንቦት 02 /2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት 08/2014 ዓ.ም)

**5. አስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ**

በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ የእለት እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ የ5ኛ ዙር እርዳታ እየገባ ነው፡፡

**6. ሌሎች አደጋዎች**

በሳምንቱ የተከሰተ አዲስ አደጋ የለም፡፡

**7. የገብያ ሁኔታ**

በሳምንቱ የዕህል ዋጋን በተመለከተ ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ነው፤ ለአብነት የጤፍ 5500 ብር፣ ማሽላ ከ2700 ብር፣ ስንዴ 2800 ብር እና በቆሎ 2150 ብር እየተሸጠ መሆኑን የክልሉ መረጃ ያስረዳል፡፡

**7.2 የእንስሳት አቅርቦት እና ዋጋን በተመለከተ**

በሳምንቱ የእንስሳት የገብያ ሁኔታ በተመለከተ ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ነው፣ ለአብነት ከፍ ያለ በሬ 80000 ብር መካከለኛ በሬ 40000 ብር፣ ላም 25000 ብር፣ በግ 4500 ብር እና መካከለኛ ፍየል 3500 ብር መሸጡን የክልሉ መረጃ ያስረዳል፡፡